# ማዕዶት




ዘከመ ተሰቅለ እግዚእነ በመልዕልተ መስቀል ።

ቁጥር ፲፩

ሚያዝያ ፲፱፻፸፰ ዓ.ም

አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

# ማዕዶት

የግል ቤተ መጻሕፍት

ቍጥር ፲፭

ሚያዝያ ፲፱፻፸፭ ዓ.ም

አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org

በክርስቶስ ትንሣኤ የሕይወት ነፃነት ተገኘ ከክርስቶስ ትንሣኤ በፊት የሰው ሁሉ የሕይወቱ ፍጻሜ ፡ ሞት እንደሆነ ይገመት ነበር ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ ግን ከሞት በኋላ ዘለዓለማዊ ሕይወት እንዳለና አስቀድመው የሞቱ ወደ ፊትም የሚሞቱ ሁሉ እንደሚነሡ በክርስቶስ ትንሣኤ ተረጋገጠ ክርስቶስ በኩረ ትንሣኤ ሆኖ ተነሥቶአልና ።

የክርስትና እምነት ዛሬ ካለበት ሊደርስ የቻለው በክርስቶስ ትንሣኤ እውነትነት ነው ክርስቶስ ባይነሣ ኖሮ የክርስትና እምነት ባልቀጠለም ነበር ነገር ግን ክርስቶስ በእውነት ስለተነሣና ሕያው አምላክ ስለሆነ የክርስትናም እምነት ሕያው ሆኖ ይኖራል ።

ክርስቶስ በሞተ ጊዜ ጠላቶቹ ተደሰቱ ደቀ መዛሙርቱ አዘኑ ። ነገር ግን በሦስተኛው ቀን በተነሣ ጊዜ ጠላቶቹ አፈሩ ፤ ደቀ መዛሙርቱ ግን ተጽናኑ በአዩትም ጊዜ እጅግ ተደሰቱ ፤ ክርስቶስን ከሙታን ተነሥቶ ከአዩት በኋላ ዳግመኛ ሞትን አልፈሩም በእርሱ ትንሣኤ የራሳቸውንም ትንሣኤ አረጋግጠዋልና ።

የተወደዳችሁ ምእመናን እነሆ ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ወዲህ ሁል ጊዜ በየዓመቱ ከስቅለት ዓርብ በኋላ ፋሲካን እናከብራለን በዚህም ከኃዘን በኋላ ደስታ ከሞት በኋላ ሕይወት መኖሩን እናስታውሳለን ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ በመስቀል ላይ መሰቀሉ ፤ ሕማምንና ሞትን መቀበሉ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር ማደሩ የሰው ልጆችን ሁሉ ከሞት ወደ ሕይወት ፤ ከኃሣር ወደ ክብር ከጨለማ ወደ ብርሃን ለማውጣትና ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ለማዳን ፍቅሩ ፤ ርኅራኄውና ቸርነቱ ስለአስገደደው ነው ።

ስለዚህ በክርስቶስ ክርስቲያን በወልድ ወሉድ የተባልን ሁሉ የሕያው ክርስቶስን ትንሣኤ በምናከብርበት ዕለትና በማናቸውም ሰዓት በልዩ ልዩ ምክንያት ችግር ለደረሰባቸው ወገኖቻችን ሁሉ ልናዝንላቸው ፤ ልንራራላቸውና በፍቅር ልንመለከታቸው ይገባል ። ክርስቶስ ራሱን የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ ላቀረበላቸውና ለሞተላቸው ወገኖች ልናስብላቸው ያስፈልጋል ።

ይህንንም ለማድረግ ሕያው አምላክ የትንሣኤውን ብርሃን በልቡናችን ያብራልን የሰላም አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለም ሁሉ ሰላምን ይስጥ ። ሀገራችን ኢትዮጵያን ለዘለዓለም ይባርክ ።



# ከበለስ ምን ይጠበቃል?

ከሌላው ማግኘትን ፤ መቀበልን የሚፈልግ ፍጡር ሁሉ ሌላውም ከርሱ እንዲህ ያለውን ሁኔታ ይጠበቃል ምክንያቱም የተፈጥሮ ሕግ ነውና ። ለምሳሌ ከአትክልቶች ብንነሣ ተክይ ያስፈልጋቸዋል ለመብቀል ዝናብ ለምግብ አፈር ለሙቀት የፀሐይ ብርሃን ሕይወትና ዕድገት የሚሰጥ አየር ያሻቸዋል ። እነሱ ይህንን ከሌላው የሚጠብቁ ከሆነ ከእነሱም የሚጠበቅ አለ ማለት ነው ።

ይህም ሲባል ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች ጠብቆ ካገኘ ከመልካም የወይን ግንድ ጣፋጭ እንጂ መራራ ወይም ኮምጣጣ ፍሬ አይጠበቅም እንዲሁም ከበለስ ዛፍ ፍሬ እንጂ ኮምጣጣ ፍሬ አይጠበቅም ። ይህ ከሆነ ዓላማን እንደመርሳት ያስቆጥራል ተግባርንም መዘንጋት ነው ።

መቼም የተነሣነው የበለስን ሁኔታ ለማወቅ ነው ። ታዲያ ነገርን ነገር ያነሳዋልና እንዲያው ለመሆኑ እርስዎን እርበዎት ያውቃል? ከከተማ ወደ ገጠር በሚጓዙበት ጊዜ ይደክመዎታል ይርብዎታል በኪስዎ ሳንቲም ቢኖርም የሚገዛ ምግብ አያገኙም በመጨረሻ ትዝ ይለዎትና በገጠር ጓደኛ እንዳለዎት ያስባሉ እንደምንም ጠይቀው ከቤቱ ይደርሳሉ ጓደኛዎንም በማግኘትዎ ደስ ይለዎታል በደስታም ተቀብሉ ወደ ቤቱ ያስገባዎታል ካሁን ካሁን ምግብ አቀረበልኝ እያሉ ሲጠባበቁ የጓደኛዎ ባለቤት ትመጣና ወጥ አለ እንጀራ ግን አልቋል ብትል ይመርቋታል? ወይስ ይረግሟታል? ደስታ ወይስ ኃዘን ይሰማዎታል? በጣም ርቦታልና እያዘኑና እየተራገሙ እንደሚሄዱ ግልጽ ነው

በዚህ አንጻር የተፈጸመ ድርጊት ይሄውና ክርስቶስ ለማስተማር ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ገጠር ተጓዘ ጉዞውንም ፈጽሞ ወደ ከተማ ሲመለስ ተራበ በመንገድም አጠገብ በለስ አይቶ ወደ እርስዋ መጣ ከቅጠልም ብቻ በቀር ምንም አላገኘባትምና «ለዘላለሙ ፍሬ አይገኝብሽ»አላት።በለሲቱም ያንጊዜውኑ ደረቀች ደቀ መዛሙርቱም ይህን አይተው በለሲቱ ያንጊዜውኑ እንዴት ደረቀች! ብለው ተደነቁ (ማቴ ፡ ፳፩ ፡ ፲፰-፳ ። )

በለሲቱን ክርስቶስ የረገማትና እንድትደርቅ ያደረጋት ብቁ ምክንያት ነበር ። ይኸውም አንደኛ ለሌሎች ዕፀዋት በየጊዜው የሚደረገው ቸርነት በረከትና ፤ ስጦታ ሁሉ ለርስዋ አላጎደለባትም ። ሁለተኛው ጊዜው የቅጠል ሳይሆን የፍሬ ወራት ነበር ሦስተኛ ዛፎች ሁሉ ፍሬያቸውን የሚሰጡበት ወቅት ሲሆን በለሲቱ ግን ከቅጠል በቀር ፍሬ ልታስገኝ አልቻለችም ይህን በመሰለው ጉድለትዋ ጥፋትና እርግማን ሊደርስባት ችሏል ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ላይ በተመላለሰበት ወቅት ግልጽ ሆነው የሚታዩ ብዙ ምሳሌዎችን ተናግሮ ነበር ። ከምሳሌዎቹም መካከል ከላይ የጠቀስናት የበለሲቱ ዛፍና የወይኑ እርሻ ይገኙበታል ። የበለሲቱ ዛፍ የቤተ እስራኤል ምሳሌ ስትሆን የወይኑ እርሻ ደግሞ የአይሁድ ሕዝብ ምሳሌ ነው ። የበለሲቱ ምሳሌ የሆነችው ቤተ እስራኤልም የአይሁድ ሕብረተሰብ የሚኖሩባት አገር ፓልስታይን ስትሆን ዋና ከተማዋ ኢየሩሳሌም ነው

የጠፋውን የሰውን ሕይወት ለመፈለግና ለማዳን የመጣው ክርስቶስ ተርቦ ፍሬ ለመፈለግ ወደ በለስዋ እንደሄደ ሁሉ የበጎ ነገር ፤ የምግባር ፤ የሃይማኖት የጽድቅ ፍሬ ለመፈለግ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ ። ታላቂቱዋ የኢየሩሳሌም ከተማ አሻግረው ሲመለከቱዋት ለምልማና አብባ ትታያለች ውስጡዋን ግን ሲገቡ በአመጽ ፤ በኃጢአት ፤ በክፋት ፤ በተንኮል ፤ በነፍስ ግዳይ ፤ በፍርድ ጉድለት ፤ በዝርፊያና ፤ በንጥቂያ ከመሞላቱዋም በላይ ከሞራል ውድቀት በቀር የተጠበቀባትን የጽድቅና የሰላም ፍሬ ለማስገኘት አልቻለችም ።

ክርስቶስ ሁኔታዋን ከተመለከተ በኋላ «ለሰላምሽ የሚሆነውን በዚህ ቀን አንቺስ ስንኳ ብታውቂ አሁን ግን ከዓይንሽ ተሰውሮአል ወራት ይመጣብሻልና ጠላቶችሽም ቅጥር ይቀጥሩብሻል ፤ ይከቡሻልም ፤ በየበኩልም ያስጨንቁሻል ፤ አንቺን በአንቺም ውስጥ የሚኖሩትን ልጆችሽን ወደ ታች ይጥላሉ ፤ በአንቺ ውስጥም ድንጋይ በድንጋይ ላይ አይተውም የመጎብኘትሽን ዘመን አላወቅሽምና» ሲል ረገማት ወደፊትም የሚደርስባትን ጥፋትና ታላቅ ውድቀት ነገራት(ሉቃስ ም ፡ ፲፱፡ቊ፡ ፵፪-፵፬)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው የታመሙትን ለመፈወስ የተራቡትን ለመመገብ በጠቅላላው የሰው ሕይወት የጽድቅ ፍሬ እንዲያፈራ ነበር ። ምንደኛ የሆኑት ካህናትና ጸሐፍት ግን ክርስቶስ የሚሰራው ሥራ ሁሉ ሰዎችን እንዳይጠቅም እና የፍቅር ሙቀት እንዳይሰጥ በተንኮላቸው ያጨልሙት ነበር በሰው ልብ ላይ የሚዘራውም የወንጌል ትምህርት በቅሎ ፍሬ እንዳይሰጥ እንደሾህ እያነቁ ለማስቀረት ይጥሩ ነበር በመንገድ ላይ የወደቀውን ዘር ወፍ እንደለቀመው ሁሉ እነርሱም በሰው ልብ ላይ እንዳይበቅል በተንኮላቸውና በክፋታቸው እየለቀሙ ይጥሉት ነበር ።



www.ethiopianorthodox.org

